የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስድስተኛ ዓመት q_R 08
አዲስ አበባ ሚያዝያ 4 qN 2ሺ2 ዓ.ም

bx}T×eÃ ØÁ‰§ê Ä}äK‰s}Ãê ¶pBI}K
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 18
ADDIS ABABA 12th April, 2010

¥WÅ

xê J q_R 6)%8/2ሺ2 ›.M

የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ..... ገጽ 5¹}2)07

CONTENTS

Proclamation No. 668 /2010

Disclosure and Registration of Assets Proclamation …Page 5217

xê J q_R 6)%8/2ሺ2

ሀብትን ለማሳወቅና ለማስመዝገብ የወጣ አዋጅ

ሀብትን ማሳወቅና ማስመዝገብ የመንግሥት አሠራርን በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ ለመመስረት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

የመንግሥት የሥራ ሃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሉ በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ግልጽ ሥርዓት መዘርጋት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለማስወገድ እንደሚረዳ በመታመኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ-ሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ $5 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 6)%8/2ሺ2" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION NO. 668/2010.

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DISCLOSURE AND REGISTRATION OF ASSETS

WHEREAS, the disclosure and registration of assets is important to enhance transparency and accountability in the conduct of public affairs;

WHEREAS, the disclosure and registration of assets is of paramount importance in the prevention of corruption and impropriety and helps to enhance good governance;

WHEREAS, it is necessary to put in place a transparent system that would help the conduct of public affairs and private interest go separate without intervening into one another's territory so as to avoid possible conflict of interest;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Disclosure and Registration of Assets Proclamation No.668 /2010."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "ሀብት" ማለት ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታን እና ዕዳን ይጨምራል፤

2/ "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፤

3/ "የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት የሥነ-ምግባር ሁኔታን የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል ነው፤

4/ "ተሿሚ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ ሚኒስትሮችን፣ ሚኒስትር ዴኤታዎችን፣ ምክትል ሚኒስትሮችን፣ ኮሚሽነሮችን፣ ምክትል ኮሚሽነሮችን፣ ዋና ዳይሬክተሮችንና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችን፤

ለ/ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ከንቲባዎችንና ሌሎች ተሿሚዎችን፤

ሐ/ የመደበኛና የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችን፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶችንና ዳኞችን፤

መ/ የመከላከያ ሠራዊትና ፖሊስ ተሿሚዎችን፤

ሠ/ አምባሳደሮችን፣ የቆንስላዎችና የሌሎች የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ኃላፊዎችን፤

ረ/ ዋና ኦዲተርንና ምክትል ዋና ኦዲተርን፤

ሰ/ የብሔራዊ ባንክ ገ/ና ምክትል ገ/ን፤

ሸ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን፣ ሥራ አስኪያጆችንና ምክትል ሥራ አስኪያጆችን፤

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "asset" means any movable or immovable or tangible or intangible property and includes landholdings and debts;

2/ "Commission" means the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission;

3/ "ethics liaison unit" means a unit entrusted with the duty to coordinate and advise on ethical issues in a public office or a public enterprise;

4/ "appointee" includes the following:

a) the President of the Republic, the Prime Minister, the Deputy Prime Minister, Ministers, State Ministers, Deputy Ministers, Commissioners, Deputy Commissioners, Director Generals and Deputy Director Generals;

b) Mayors and other appointees of the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

c) Presidents, Deputy Presidents and judges of regular and municipal courts;

d) appointees of the defense forces and police;

e) ambassadors, heads of consuls and other diplomatic missions;

f) the Auditor General and the Deputy Auditor General;

g) the Governor and Deputy Governor of the National Bank;

h) Members of Board of Directors, Managers and Deputy Managers of Public Enterprises;

ቀ/ የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ፕሬዝዳንቶችንና ምክትል ፕሬዝዳንቶችን።

5/ "ተመራጭ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎችን፤

ለ/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎችን፣ እና

ሐ/ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ምክር ቤቶች አባሎችን።

6/ "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

ሀ/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የመምሪያ ኃላፊነት፣ የዳይሬክተርነት፣ የአገልግሎት ኃላፊነትና ከነዚህ ተመጣጣኝና በላይ ደረጃ ያላቸው ሠራተኞችን፤

ለ/ የተሿሚዎች አማካሪዎችን፤

ሐ/ ፈቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጠር ወይም ግብር የመሰብሰብ ሥራ የሚያከናውኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን፣ ዐቃቤ ሕጎችን፣ መርማሪዎችን፣ የትራፊክ ፖሊሶችን፣ እና

መ/ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ተለይተው የሚወሰኑ ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሠራተኞችን።

7/ "ቤተሰብ" ማለት የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ ወይም በሥሩ የሚተዳደር ዕድሜው 08 ዓመት ያልሞላ ልጅ ሲሆን ጋብቻ ሳይፈጽም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የሚኖር ሰውን እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል፤

8/ "የቅርብ ዘመድ" ማለት የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ወላጆችን፣ ተወላጆችን፣ እህቶችን፣ ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፤

i) Presidents and Deputy Presidents of government higher education institutions.

5/ "elected person" includes members of :

a) the House of Peoples' Representatives;

b) the House of the Federation; and

c) the Addis Ababa and Dire Dawa city administration councils;

6/ "public servant" includes the following:

a) department heads, directors and service heads of public offices and public enterprises and other employees having equivalent or higher ranks;

b) advisors of appointees;

c) employees of public offices performing licensing, regulating or tax collection functions, prosecutors, investigators, traffic police officers; and

d) other employees of public offices and public enterprises to be specified by directives of the Commission;

7/ "family" means the spouse or a dependant child, under the age of 18, or an appointee, elected person or a public servant and include a person living together under irregular union and an adopted child;

8/ "close relative" includes ascendants, descendants, siblings and other persons related to an appointee, elected person or a public servant by consanguinity or affinity up to the third degree;

9/ "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደርና የሕግ አውጭነት፣ የዳኝነት ወይም አስፈጻሚነት የመንግሥት ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ነው፤

0/ "የመንግሥት ልማት ድርጅት" ማለት የመንግሥት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፤

01/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

02/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

9/ "public office" means any office the budget of which is fully or partially allocated by government and in which legislative, judicial or executive activities of government are performed;

10/ "public enterprise" means any public enterprise or a share company in which the total or part of the holdings is owned by government.

11/ "person" means a natural or juridical person;

12/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በፌዴራል መንግሥት እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግሥት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to appointees, elected persons and public servants of the Federal Government and the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations.

ክፍል ሁለት
ሀብትን ስለማሳወቅና ስለማስመዝገብ

PART TWO
DISCLOSURE AND REGISTRATION OF ASSETS

4. የማስመዝገብ ግዴታ

1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፡-

ሀ/ በራሱና በቤተሰቡ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ሥር የሚገኝ ሀብትን፣ እና

ለ/ የራሱንና የቤተሰቡን የገቢ ምንጮች፣

የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሀብቱን የሚያስመዘግብ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የራሱንና የቤተሰቡን ሀብትና የገቢ ምንጮች ለየብቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመሙላት ትክክለኛነቱን በፊርማው ያረጋግጣል።

4. Obligation to Register

1/ Any appointee, elected person or public servant shall have the obligation to disclose and register:

a) the assets under the ownership or possession of himself and his family; and

b) sources of his income and those of his family.

2/ The appointee, elected person or public servant who registers his assets pursuant to sub-article (1) of this Article shall fill the particulars of his assets and sources of income and those of his family in separate forms designed for such purposes and authenticate the same by his signature.

5. በምዝገባ ስለማይካተት ሀብት

1/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሀብቶች አይመዘገቡም፡-

ሀ/ በውርስ ተገኝቶ በጋራ የተያዘና ለወራሾቹ የግል አገልግሎት የሚ-ውል ንብረት፤

ለ/ የቤት እቃዎችና የግል መገልገያ-ዎች፤

ሐ/ ከጡረታ የሚገኝ ገቢ።

2/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ መሠረት በጋራ የተያዘ ንብረት በወራሾች መካከል እንደተከፋፈለ ድርሻውን አሳውቆ ማስመዝገብ አለበት።

6. ስለመዝጋቢ አካል

1/ የተሿሚዎችን፣ የተመራጮችንና የመን ግሥት ሠራተኞችን ሃብት የሚመዘግበው ኮሚሽኑ ይሆናል።

2/ ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሿሚ ዎችን፣ የተመራጮችን ወይም የመንግሥት ሠራተኞችን ሃብት እንዲመዘግብ እንደሁ ኔታው በሙሉ ወይም በከፊል የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍልን ሊወክል ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ውክለና የተሰጠው እያንዳንዱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የቀረበለትን የሃብት ማስመዝገቢያ ሰነድ ምዝገባው በተደረገ በ" ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል።

4/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከና-ወኑ የሀብት ምዝገባ ሰነዶች ጠባቂ ሆኖ ያገለግላል። ሃብታቸውን ላስመዘገቡ ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግሥት ሠራተኞች የምዝገባ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

5. Assets Exempted from Registration

1/ Notwithstanding the provisions of Article 4 of this Proclamation, the following assets shall be exempted from registration:

a) common property acquired through inheritance and held by the heirs for private use;

b) household goods and personal effects;

c) pension benefits;

2/ Any appointee, elected person or a public servant who has a share in a common property held in accordance with sub-article (1) (a) of this Article shall disclose his share for registration as soon as the property is liquidated among the heirs.

6. Body in Charge of Registration

1/ The Commission shall register assets of appointee, elected person or public servant.

2/ The Commission may delegate fully or partially as the case may be Ethics Liaison Unit to register assets of appointee, elected person or public servant when it deems it necessary.

3/ Each ethics liaison unit shall send the document of registration of assets submitted to it in accordance with sub-article (2) of Article 4 of this Proclamation to the Commission within 30 days from the date of registration.

4/ The Commission shall be the custodian of documents of registration of assets under this Article, and shall issue certificates of registration to the appointees, elected persons and public servants whose assets have been registered.

7/ ምዝገባ ስለሚካሄድበት ጊዜ

1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ከስድስት ወር በኋላ ባለው ስድስት ወር ውስጥ ሀብቱን ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት።

2/ ማንኛውም አዲስ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሀብቱን የሚያሳውቅ-ውና የሚያስመዘግበው ከተሾመበት፣ ከተመ - ረጠበት ወይም ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በ#5 ቀናት ውስጥ ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ መሠረት ሀብቱን ያስመዘገበ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ከዚያ በኋላ ሀብቱን የሚያሳውቀውና የሚያስመዘግ በው በየሁለት ዓመቱ ሆኖ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ" ቀናት ውስጥ ይሆናል።

8. የምዝገባ ጊዜን ስለማራዘም

1/ የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት የሚጠይቅ ሰው ምዝገባውን ማራዘም ያስፈለገበትን ምክንያት በጽሑፍ በመግለጽ የምዝገባ ጊዜው በተጠናቀቀ በአምስት ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማመልከት ይችላል።

2/ ኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የቀረበለት ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው የምዝገባውን ጊዜ ለአንድ ጊዜ እስከ " ቀናት ሊያራዝም ይችላል።

3/ የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ውሳኔው በደረሰው አምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል። ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።

9. ዘግይቶ ስለማስመዝገብ

በመደበኛው ወይም በተራዘመለት የማስመዝገቢያ ጊዜ ውስጥ ሀብቱን ያላስመዘገበ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ብር 1ሺ መቀጫ ከፍሎ በ" ቀናት ውስጥ ሊያስመዘግብ ይችላል።

7. Time of Registration

1/ Any appointee, elected person or public servant shall disclose and register his assets within six months after the six months from the coming in to force of this Proclamation.

2/ Any newly appointed, elected or employed person shall disclose and register the his assets within 45 days following his appointment, election or employment.

3/ Any appointee, elected person or public servant who has registered his assets in accordance with sub-article (1) or (2) of this Article shall disclose and reregister the same every two years within 30 days from the end of the budget year.

8. Extension of Time of Registration

1/ A person demanding an extension of the time of registration may establish the cause for the extension in writing and submit the same to the Commission or to the relevant ethics liaison unit within five days from the expiry of the time of registration.

2/ The commission or the relevant ethics liaison unit may, upon ascertaining that the application submitted under sub-article (1) of this Article is based on sufficient cause, extend the time of registration only once for up to 30 days.

3/ An applicant whose application for extension of the time of registration is rejected by an ethics liaison unit may apply to the Commission within five days from receipt of the decision of the ethics liaison unit. The decision of the Commission shall be final.

9. Late Registration

If an appointee, elected person or a public servant fails to register his assets within the normal or extended period of registration, he shall pay a fine of Birr 1,000and register his assets within 30 days.

0. ከስንብት በኋላ ስለሚከተሉ ግዴታዎች

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል ወይም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ሀብቱን በ" ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታ ተያ ክፍል እንዲሁም ከሁለት ዓመት በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት።

01. የምዝገባን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በተሿሚ፣ በተመራጭ ወይም በመንግሥት ሠራተኛ በተሞላ መረጃ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ የያዘ መሆኑን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ወይም ሀብቱ በትክክል አልተመዘገበም የሚል ጥቆማ ሲቀርብ ወይም በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት ምርመራ ሲጀመር የምዝገባውን ትክክለኛነት የማጣራት ተግባር ያከናውናል።

2/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የማጣራት ተግባር ሲያከናውን፡-

ሀ/ ጉዳዩ የሚመለከተው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ቀው፣

ለ/ የተሿሚውን፣ የተመራጩን ወይም የመንግሥት ሠራተኛውን ሀብት የሚመለከት መረጃ ያለው ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው መረጃውን እንዲሰጥ ሊያዘው፣ እና

ሐ/ የዋና ኦዲተርን ወይም የሌላ አግባብነት ያለውን አካል ሙያዊ ድጋፍ ሊጠቀም፣

ይችላል።

3/ ኮሚሽኑ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ መቅረቡን በማስረጃ ሲያረጋግጥ ጥፋት በፈጸመው ሰው ላይ በህጉ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል።

10. Post Employment Obligations

Any appointee, elected person or a public servant who has retired or terminated his service on any ground shall disclose his assets to the Commission or the concerned ethics liaison unit within 30 days from the date of his retirement or termination of service and finally to the commission after two years.

11. Verification of Registration

1/ The Commission shall undertake a verification process on the information submitted by an appointee, an elected person or a public servant in accordance with sub-article (2) of Article 4 of this Proclamation where it has sufficient ground to suspect the submission of incomplete, inaccurate or false information or where information is received on the inaccuracy of the registration or a criminal investigation is underway.

2/ The Commission may, in the course of verification process under sub-article (1) of this Article:

a) require the concerned appointee, elected person or public servant to produce additional information and clarification of the issue;

b) order any bank, financial institution or any other person having information regarding the assets of the concerned appointee, elected person or public servant to furnish such information; and

c) avail itself of the professional assistance of the Auditor General or any other relevant body.

3/ Whenever the Commission ascertains, with evidence, the existence of incomplete, inaccurate or falsified information, it shall cause necessary measures to be taken upon the culprit according to the law.

02. <u>የምዝገባ መረጃ ተደራሽነት</u>

1/ በኮሚሽኑ እጅ የሚገኝ ማንኛውም የተ ኸሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የሀብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ክፍት ይሆናል።

2/ ስለሀብት ምዝገባ መረጃ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጥያቄውን በጽሁፍ ለኮ ሚሽኑ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሊያቀ ርብ ይችላል።

3/ ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የምዝገባውን መረጃ ለጠየቀው ሰው መስጠት አለበት።

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የቤተሰብ ሀብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለፍትህ ሥራ ወይም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚወስነው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር የሚያዝ ይሆናል።

5/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በየሁለት ዓመቱ ስላከናወነው የሀብት ምዝገባ አጠቃላይ መረጃ በሪፖርት መልክ ያወጣል።

03. <u>የሃብት አለመመዝገብ የሚያስከትለው ውጤት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ ማናቸ ውም የተኸሚ፣ የተመራጭ ወይም የመን ግሥት ሠራተኛ ሀብት ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 4)09/2/ ድንጋጌ አፈጻጸም ሲባል ምንጩ እንዳልታወቀ ንብረት ይቆጠራል።

<u>ክፍል ሶስት</u>
<u>የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅና ስለማስወገድ</u>

04. <u>መ ር ህ</u>

ማንኛውም ተኸሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የያዘውን መንግሥታዊ የሃላፊነት ቦታ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል አለበት። በማንኛውም ምክንያት ቢሆን በሥራው አጋጣሚ ያገኘውንና ሕዝብ እንዲያውቀው ያለተደረገን መረጃ ለግል ጥቅሙ ማዋል የለበትም።

12. <u>Accessibility of Registered Information</u>

1/ All information regarding the registration of assets of an appointee, elected person or a public servant shall be open to the public.

2/ Any person who wishes to access information regarding the registration of assets may apply in writing to the Commission or to the concerned ethics liaison unit.

3/ The Commission or the concerned ethics liaison unit shall accept and grant the information requested to the requesting person.

4/ Notwithstanding the provisions of this Article the information regarding the registration of family assets shall be confidential unless disclosure is required in the interest of justice or for other purposes to be determined by the Commission as necessary.

5/ The Commission shall provide the public with general information regarding the registration of assets under this Proclamation every two years by way of reports.

13. <u>Effect of Non-Registration of Assets</u>

Any asset of an appointee, an elected person or a public servant not registered in accordance with this Proclamation shall, in the absence of proof to the contrary, be considered as an unexplained property for the purpose of applying the provisions of Article 419(2) of the Criminal Code.

<u>PART THREE</u>
<u>DISCLOSURE AND AVOIDANCE OF CONFLICT OF INTEREST</u>

14. <u>Principle</u>

Any appointee, elected person or a public servant shall use the public office to which he is entrusted to protecting the public interest alone. On no account shall he secure personal gain from the information brought to his knowledge as a result of his assumption of public office and not made public.

05. ስጦታ፣ መስተንግዶና የጉዞ ግብዣ

1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የመወሰን ሥልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል የለበትም።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም የቀረበለትን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ያለመቀበል በስራ ግንኙነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስጦታውን፣ መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለመቀበል ይችላል። ሆኖም የተቀበለውን ስጦታ አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ገቢ ማድረግ ወይም መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማሳወቅ አለበት።

06. የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ

1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ሃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ሊያስከትልበት የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡-

ሀ/ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ወይም አስተያየት ከመስጠት እንዲሁም ከኃላፊነቱ ጋር የማይጣጣም ወይም ታማኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ማንኛውንም ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ፣ እና

ለ/ ሁኔታውን ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ፣

አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የጥቅም ግጭት ሊከሰት መቻሉ የተገለጸለት የበላይ ኃላፊ እንደሁኔታው ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳዩን ማየቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሊሰጠው ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል።

15. Gift, Hospitality and Sponsored Travel

1/ Any appointee, elected person or a public servant may not accept any gift, hospitality or sponsored travel that may put his authority to decide under question or ensue conflict of interest.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, if refusal to accept a gift, hospitality or sponsored travel may jeopardize working relation, an appointee, an elected person or a public servant may accept the gift, hospitality or sponsored travel; provided, however, that he shall deposit the gift with the relevant public office or public enterprise or disclose the hospitality or sponsored travel to the Commission or the relevant ethics liaison unit.

16. Measures to be Taken to Avoid Conflict of Interest

1/ Where an appointee, an elected person or a public servant encounters a case that may lead to a conflict between his official duty and his own or his close relative's private interest, he shall:

a) refrain from giving decision or opinion on the case as well as from taking any action that may be inconsistent with his official duty or may compromise his loyalty; and

b) disclose the situation to the concerned higher official.

2/ A higher official who has received a disclosure under sub-article (1) of this Article may instruct the appointee, elected person or public servant to continue handling the case or may delegate another person instead, as the case may be.

07. <u>የጥቅም ግጭት መከሰቱን ተከትሎ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ሃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በበላይ ኃላፊው ሲጠየቅ ጥፋተኛ መሆኑን በይፋ አምኖ ይቅርታ የመጠየቅ ወይም ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ አለበት።

08. <u>ከሥራ መልቀቅ በኋላ ስለሚኖር ክልከላ</u>

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራ በለቀቀ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሲቆጣጠራቸው ከነበረው ሰዎች ጋር ጥቅም የሚያስገኙ ሥራዎች መሥራት የለበትም። ዝርዝሩ በደንብ እና /ወይም/ በመመሪያ ይገለጻል።

09. <u>የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ ግዴታን ስላለመወጣት</u>

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን በዚህ አዋጅ መሠረት የማሳወቅ ግዴታውን ካልተወጣ አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል።

<u>ክፍል አራት</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

!. <u>ጥቆማ ስለማቅረብ</u>

1/ ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ጥሷል በሚለው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ጥቆማ ማቅረብ ይችላል።

2/ ጥቆማው እስከተቻለ ድረስ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር በፅሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ይቀርባል።

3/ በቀረበው ጥቆማ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የምርመራ ሂደቱና መዛግብቱ በሚስጠር ተይዘው ይቆያሉ።

17. <u>Measures to be Taken Following the Event of Conflict of Interest</u>

Any appointee, elected person or public servant shall, following any event of conflict between his official duty and his own or his close relative's private interest, publicly admit his fault and ask for apology or resign from office, on his own initiative or when required by his superior to do so.

18. <u>Post Employment Limitation</u>

Any appointee, elected person or public servant may not take up any benefit ensuing work from persons whom he used to control, until two years after leaving office. The details shall be provided in regulations and/or directives.

19. <u>Failure to Disclose Conflict of Interest</u>

An appropriate administrative sanction shall, in accordance with the relevant code of ethics, be taken against any appointee, elected person or public servant who fails to disclose any conflict of interest in accordance with this Proclamation.

<u>PART FOUR</u>
<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

20. <u>Whistle-blowing</u>

1/ Any person may file whistle-blowing against an appointee, an elected person, or a public servant for breaching this Proclamation.

2/ A whistle-blowing shall be submitted, in writing, to the commission or the relevant ethics liaison unit and, as much as possible, be accompanied with supporting evidence.

3/ The investigation process and related documents shall be kept confidential until final decision is taken on the whistle-blowing.

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ጥቆማ የተገኘው መረጃ በወንጀል ህግ አንቀጽ 4)09/2/ የሀብት መወረስ ውሳኔ ለማሰጠት ካስቻለ የተወረሰው ሀብት ከሚያስገኘው ገቢ ውስጥ !5 በመቶ ለጠቋሚው ይከፈላል።

!1. <u>የአዋጁን ተፈጻሚነት ስለማረጋገጥ</u>

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ፡-

1/ ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግሥት ሠራተኞች ሀብታቸውን በወቅቱ እንዲያስ መዘግቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

2/ አግባብ ያላቸው የሥነ-ምግባር ደንቦችን አውጥቶ ተፈጻሚ ያደርጋል።

!2. <u>ቅ ጣ ት</u>

1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፡-

ሀ/ ሀብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ የምዝገባ መረጃ ከሰጠ፣ ወይም

ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላ - ለፍ ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ከተቀበለ ወይም የተቀበለውን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ሳያሳውቅ ከቀረ፣

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 4)07 መሠረት ይቀጣል።

2/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ! መሠረት ለኮሚ- ሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ጥቆማ አቅርቧል ወይም ምስክ- ርነት ሰጥቷል ወይም ጥቆማ ለማቅረብ ወይም ምስክርነት ለመስጠት ተዘጋጅ- ቷል በሚል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበቀል እርምጃ የወሰደ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 4)#4 መሠረት ይቀጣል።

4/ If the information obtained through whistle-blowing leads to the confiscation of assets under Article 419(2) of the Criminal Code, the whistle-blower shall be entitled to 25% of the proceeds of the confiscated asset.

21. <u>Assuring Compliance</u>

Any public office or public enterprise shall, to ensure compliance with this Proclamation:

1/ facilitate the timely registration of assets of appointees, elected persons and public servants;

2/ issue and enforce relevant code of ethics.

22. <u>Penalty</u>

1/ Any appointee, elected person or public servant who:

a) fails to disclose his assets for registration in accordance with this Proclamation or intentionally submits incorrect disclosure; or

b) in contravention of this Proclamation, accepts a gift, hospitality or sponsored travel, or fails to disclose any gift, hospitality or sponsored travel he has accepted;

shall be punished in accordance with Article 417 of the Criminal Code.

2/ Any appointee, elected person or public servant who directly or indirectly takes any reprisal measure against a whistle-blower or witness for submitting whistle-blowing or giving witness or is about to submit whistle-blowing or give testimony to the Commission or ethics liaison unit pursuant to Article 20 of this Proclamation shall be punished in accordance with Article 444 of the Criminal Code.

3/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሳያሣውቅም ሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 06 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ተፈቅዶለት ሲሠራ የመንግሥት ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የራሱን ወይም የቅርብ ዘመዱን የግል ጥቅም ያራመደ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል።

4/ ማንኛውም ሰው በክፉ ልቦና በመነሳሳት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ጥቆማ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ! መሠረት ካቀረበ እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ወይም እስከ ብር 2ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

3/ Any appointee, elected person or public servant who, either without disclosing the existence of conflict of interest or acting upon being authorized in accordance with sub-article (2) of Article 16 of this Proclamation, uses his official duty to promote his own or his close relative's private interest shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

4/ Any person who maliciously submits unfounded whistle-blowing pursuant to Article 20 of this Proclamation shall be punished with imprisonment not exceeding three years or with a fine not exceeding Birr 2,000 or both.

!3. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ህግ ወይም ማንኛውም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

23. Inapplicable Laws

No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

!4. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

2/ ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

24. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Commission may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

!5. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

25. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

አዲስ አበባ ሚያዝያ 4 ቀን 2ሺ2 ዓ.ም

Done at Addis Ababa, this 12th day of April , 2010

GR¥ wLdg|×Rg|S

GIRMA WOLDEGIORGIS

yx|T×eÃ ØÁ‰§ê| Ä|ä K‰s|Ãê|
¶pBl|K PÊz|ÄNT

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA